ግንቦት 2002

# *ምርጫ ከሚደገም 66 ይደገም*

አምባ ገነኑ እና ዘረኛ የወያኔው ቡድን በሰሞኑ ተደረገ በተባለው ቲያትራዊ ምርጫ እራሱን ሙሉ በሙሉ አሸናፊ አድርጎ ፤ አዳማቂዎችን ጠራርጎ የከረፋ ስርዓቱን ሲያፐነን መገርም ሳይሆን ትልቅ ትምህርት ወስደን ትክክለኛ ዲሞክራሲያዊ ለውጥ ለኢትዮጵያ ለማምጣት ሁላቸንም በአንድ መንፈስ **"ትክክለኛ ስልጣን ለኢትዮጵያ ሰፊው ሕዝብ "** የሚለውን መፈክር በትግል በማጀብ መነሳትና መደራጀት ይኖርብናል።

ኢወክንድ ከመጀመርያውም ጀምሮ በወያኔ ቁልፍ ከሚከፈትና ከሚዘጋ ግዑዝ የምርጫ ቦርድና፣ ሕገ ደደቢት ከሆነው የምርጫ ሕግ የሚወለደው ወያኔ እንጅ ሌላ ባለመሆኑ አስቀድሞ ምርጫው የተበላ እቁብ ሲል ሰይሞት እንደነበር ይታወቃል። ለብለን ነበር ጊዜ ባናጠፋም።

ኢወክንድ አንጋፋ ወላዲውን የኢሕአፓን የጠራ አቋምን ይከተላልና ይህ መስመር የሳተ የምርጫ ቧልት ቲያትራዊ እንጅ ነፃ አለመሆኑን በማረጋገጥ ይልቅስ ነፃነት የሻታችሁ ሕዝባዊ መንግስት ያላችሁ አብረን ገጥመን በሁለንተናዊ ትግል ይህን ተውሳክ ስርዓት ከሕዝባችን ላይ ነቅለን ከስቃይ እናድነው ስንል ነበር ደጋግመን ጥሪ ያሰማነው።

ኢወክንድ ከሁሉም ጠንካራ ነገር ካለችው ትምህርት እንደሚወስድ ሁሉ በወቅታዊ ሆያሆዬ ተፈጥረው ሆያሆዬው ሲያልፍ ከአዲስ ዘመን መድረስ እያቃታቸው ከሚፍረከረኩትም ከውድቀታቸው ትምህርት ይወስዳልና ሊጋዎች ብንሆንም በቀድምቶቻችን የመሰዋእትነት ማጥንት ታጥነናልና የወያኔን የምርጫ ቧልት ኢሕአፓን ተከትለን በምክንያት አወገዝነው እንጅ በ 30 ዲናር ተሸጠን በወያኔ ዘፈን መስቀል አደባባይ እስክስታ አለማለታችን ሕዝባዊ ኩራት ይሰማናል።

እኛ የኢትዮጵያውያኑን ወጣት ሊግ ስናቋቁም ወያኔ በላያችን ላይ ሊግ ለመደረብ ወራት ባይፈጅበትም ግና የወጣቱን ልብ በፍቅር ሳይሆን በገንዘብ ገዝቶ መለሰ በቁሙ በሳጥን ታሽጎ ሲያጣጥር ዳንኪራ ከመርገጥ በላይ ስላልገፋ ነፃነታቸውን በዲናር ለሸጡ የገኘው ወያኔ ወጣት ሊጎችን እግረ መንገዳችን ይሄ ነው ሊግሽ አፈርንብሽ የሚለውን መልእክት እናስተላልፋለን።

ፓርላማ ቢገቡ ከመወዘፍ ግፋ ሲልም ይመዝገብልኝ ከማለት ለማይዘሉ ተቃዋሚ የተባሉት በመሸንቀጠራቸው ዳንኪራ ባንረግጥም ከንፈር ግን አንመጥም። ኢወክንድ ድሮም ለገማው ወያኔ ጊዜያዊ የመከላከያ ማጥንት ነበራችሁ እንጅ የሕዝብን ድምፅ ያስበላችሁ በሙሉ እንኳን ለዳግማዊ ውርደት ተዳረጋችሁ ስንል እውነተኛ ሕዝባዊና ሀገራዊ ምርጫ ምን እንደሆነ ኢወክንድ በክንዱ እስኪያሳያችሁ ድረስ ምርጫ ይደገምልን በሚለው ቧልት አትዳክሩ ነው የምንል።

የኢትዮጵያ ወጣት በ30 ብር ነፃነቱን አይሸጥም

ምርጫው ከሚደገም 66 ይደገም

Tel 202-291-5832 P.O.Box 56068 Washington DC 20040 e-mail: join@eprpy.com
www.eprpy.com